# የኮቪድ-19 ፈጣን መመርመሪያዎች

Maryland's Largest School District
**MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS**
*Expanding Opportunity and Unleashing Potential*

## አንዱ አስፈላጊ የኮቪድ-19 ወረርሽኝ የሚቀንስበት ስትራቴጂ ወደ ቤት የሚወሰዱ የኮቪድ ፈጣን መመርመሪያዎችን መጠቀም ነው።

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በሚቀጥሉት ሁለት ወራት በቤት ውስጥ የሚጠቀሙባቸውን ፈጣን የአፍንጫ (ፈሳሽ) የኮቪድ መመርመሪያዎችን ለማከፋፈል አቅዷል።

- በእያንዳንዱ እሽግ ውስጥ ሁለት መመርመሪያዎች ይገኛሉ።
- በቤት ውስጥ የሚደረጉት ምርመራዎች በ 15 ደቂቃ ውጤት የሚሰጡ ፈጣን የኮቪድ-19 አንቲጅን ያላቸው ሲሆን አንድ ግለሰብ የሕመም ምልክቶች እያጋጠመው እንደሆነ ወይም እንዳልሆነ መጠቀም ይችላሉ።

## መቼ ምርመራ ማድረግ እንደሚያስፈልግ

### ተማሪ

- አንድ ተማሪ በኮቪድ-19 መያዙን ከተረጋገጠ ሰው ጋር የቅርብ ንክኪ ያደረገ(ች) ከሆነ—ከተጋለጠ(ች)በት 5 ቀናት በኋላ ፈጣን ምርመራ ማድረግ ያስፈልጋል።
- ያልተከተበ(ች) ተማሪ ኳራንቲን ሲቆይ/ስትቆይ—በ 6ኛው ቀን ወደ ትምህርት ቤት ከመመለሱ(ሷ) በፊት በ 5ኛው ቀን ፈጣን ምርመራ ማድረግ ያስፈልጋል።
- አንድ ተማሪ የኮቪድ-19 ምልክቶች ሲያጋጥመው ወይም ሲያጋጥማት—ምልክቶቹ እንደጀመሩ ወዲያውኑ ፈጣን ምርመራ ማድረግ ያስፈልጋል።
- ከጉዞ ወይም ከትልቅ ስብሰባዎች መልስ—ወደ ትምህርት ቤት ከመመለሳችሁ በፊት ፈጣን ምርመራ ማድረግ ያስፈልጋል።

### ሠራተኛ

- የሰራተኛ አባል የምርመራ ውጤት ፖዚቲቭ ሆኖ ከተገኘ—ከኳራንቲን በኋላ ከ 6ኛው ቀን በፊት ራስን ማግለል ያበቃ እንደሆነ ለማረጋገጥ በ 5ኛው ቀን ፈጣን ምርመራ መውሰድ ያስፈልጋል።
- የሰራተኛ አባል የኮቪድ-19 ምልክቶች ሲያጋጥም—ምልክቶቹ ሲጀምሩ ወዲያውኑ ፈጣን ምርመራ መውሰድ ያስፈልጋል።
- የሰራተኛ አባል በቅርብ ጊዜ ንክኪ ምክንያት ኳራንቲን ሲሆን—ከ6ኛው ቀን በፊት ኳራንቲኑ ሊያበቃ ይችል እንደሆነ ለማረጋገጥ ከኳራንቲ በኋላ በ 5ኛው ቀን ፈጣን ምርመራ ማድረግ ያስፈልጋል።
- ከጉዞ ወይም ከትልቅ ስብሰባ መልስ—ወደ ትምህርት ቤት ከመመለሳችሁ በፊት ፈጣን ምርመራ ያድርጉ።

## የኮቪድ-19 ምርመራ ውጤት እንዴት በይነመረብ ላይ ማስተላለፍ እንደሚቻል

እንዲሁም የሪፖርት ማቅረቢያ ቅጹን እርስዎ በሚጠቀሙበት ስማርት ዲቫይስ ላይ ለመጫን ከዚህ በታች ያለውን የ QR ኮድ መጠቀም ይችላሉ።

**ደረጃ 1** የኮቪድ-19 ሪፖርት ማቅረቢያ ቅጽ ላይ ጠቅ ያድርጉ
bit.ly/MCPS-Reporting-Form

**ደረጃ 2** የምርመራ ውጤቱን ሪፖርት ለማቅረብ ቅጹን ይሙሉ

**ደረጃ 3** አማራጭ፡- በምርመራ ውጤቱ ላይ የሚታየውን ይግለጹ።